## Social: በጥበቃ ሥር ያሉ የዱር እንስሳት ለችግርና ለሞት እየተዳረጉ ነው

በተወሰነ ሥፍራ /ዙ ውስጥ/ ተጠብቀው ያሉትን የዱር እንስሳት በአግባቡ ለመያዝና ለማስተዳደር የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች ባለመሟላታቸው የአሰራር መመሪያዎችም ባለመኖራቸው የተነሳ የዱር እንስሳቱ ለችግርና ለሞት እየተዳረጉ መሆናቸውን ዶ/ር አሰፋ መብራቴ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ባለሙያዎች ማኅበር ገለፁ፡

በርካታ አቦሸማኔዎች፣ አናብስትና ሌሎችም የዱር እንስሳት ከሚኖሩበት አካባቢ በሕገ ወጥ መንገድ እየተወሰዱ መሆናቸውን የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ዶ/ር አሰፋ አመልክተው ይህ አይነቱ ሕገ ወጥ ድርጊት በአስቸኳይ መቆም እንዳለበት አሳስበዋል።

በእነዚህ ችግሮችና በጥበቃ ውስጥ ባሉት የዱር እንስሳት አያያዝ ዙሪያ የሚነጋገር ስብሰባ ሰኞ ኅዳር 25 ቀን 1999 ዓ.ም በግብርና ምርምር ድርጅት አዳራሽ እንደሚካሄድ ተጠቁሟል።

ስብሰባውን ከግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት መምሪያ፣ እንዲሁም አፍሪካን ፖርክ ከተባለው የግል ድርጅት ጋር በመተባበር ያዘጋጀው መሆኑን ዶ/ር አሰፋ አመልክተዋል።

Source: Ethiopian Reporter